# የማግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 242/2013
# ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አውጭው ባለስልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010 አንቀጽ 65(2) በተሰጠው ስልጣን ማስረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 242/2013 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት በዚህ መመሪያ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጣቸው በስተቀር በአዋጁ የተሰጠቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ወስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የመንግስትና የግል አጋርነትን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 1076/2010 ነው፡፡
2. "በመንግስት የሚደረግ ድጋፍ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 47 መሠረት በመንግስት የሚሰጥ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ወይም ዋስትና ነው፡፡
3. "የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተወካይ" ማለት በፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ወስጥ እንዲያገለግል በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የሚመደብ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተወካይ ነው፡፡
4. "የመግአ ፕሮጀክቶች ዝርዝር" ማለት በመግአ አሰራር እንዲተገበሩ የታመነባቸው በቅደም ተከተል የተቀመጡ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ነው፡፡
5. "የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን" ማለት በመግአ አዋጅ አንቀጽ 14 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ማስረት በተዋዋይ ባለስልጣን የሚቋቋም ቡድን ነው፡፡
6. "የፕሮጀክት አፈጻጸም መከታተያ ሰነድ" ማለት የፕሮጀክት አፈጻጸምን በመከታተል ተዋዋይ ባለስልጣንና የግሉ ባለሀብት በፕሮጀክት ስምምነቱ መሠረት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲረዳ በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የሚዘጋጅ ዝርዝር የፕሮጀክት አፈፃፀም ማለኪያዎችን የያዘ ሰነድ ነው፡፡

### 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው የመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የመንግስትና የግል አጋርነት አስተዳደር

## 5. የመንግስትና የግል አጋርነት ቦርድ

1. ቦርዱ ዘጠኝ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ሰባቱ ከመንግስትና ሁለቱ ደግሞ ከግሉ ዘርፍ የሚወከሉ ይሆናል፡፡

2. የቦርዱ ሰብሳቢ በቦርዱ ወስጥ የግሉን ዘርፍ የሚወከሉ ተወካዮች እንዲሚጡ በማድረግ የግሉ ዘርፍ ወክልና በቦርዱ ወስጥ መሟላቱን ያረጋግጣል፡ -

   ሀ/ የቦርድ ሰብሳቢ በቦርዱ ወስጥ የግሉን ዘርፍ እንዲወክሉ የሚሾሙ ግለሰቦች ያላቸውን ሚና፣ በግል የንግድ ድርጅቶች ወስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ወይም የኃላፊነት ደረጃ፣ በኩባንያዎች ወስጥ ያላቸውን አክስዮን ወይም ሌሎች ጥቅሞች እና የሚከጡት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ካለ እንዲያሳወቁ ይጠይቃል፡፡

   ለ/ በየጊዜው ሊታደስ የሚችል ሆኖ የግሉን ዘርፍ የሚወክሉ ግለሰቦች የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡

3. ከግል ዘርፍ የተወከሉ የቦርድ አባላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ላይ የተጠቀሱትን የስነ-ምግባር ግዴታዎች መጣሳቸው ከተረጋገጠ ያለማስጠንቀቂያ በማንኛውም ጊዜ ከአባልነት ሊነሱ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ከመንግስት የተወከሉት የቦርድ አባላት ተመሳሳይ የስነ-ምግባር ጥሰት ሲፈጽሙ በመንግስት አሰራር ስርዓት ማሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

4. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በማንኛውም የቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ድምጽ የማይሰጥ ሆኖ ይሳተፋል፡፡

## 6. የመንግስትና የግል አጋርነት ቦርድ ስብሰባ

1. የቦርዱ ወሳኔዎች በጽሑፍ የሚደረጉ ሆነው ሁሉም የቦርድ ወሳኔዎች በስብሰባው ወቅት መተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

2. ቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎቹን በየሶስት ወሩ ያደርጋል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የቦርዱ ሰብሳቢ በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

3. የቦርድ ስብሰባ ማሳወቂያ ደብዳቤ የስብሰባወን አጀንዳ፣ ቦታና ሰዓት መግለጽ አለበት፡፡ ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልተስማማ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ካልተወሰነ በስተቀር የቦርዱ ስብሰባ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወስጥ ይካሄዳል፡፡

4. በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ሰብሳቢወን ጨምሮ ቢያንስ ስድስት የቦርዱ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጥራል፡፡

5. የመንግስትን ተቋማት የሚወክሉ የቦርዱ አባላት ሚኒስትር ወይም የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

6. እንደየሁኔታው የቦርዱ አባላት የቦርዱ ስብሰባ ላይ በአካል ወይም ተስማሚ የኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው ባሉበት ሆነው መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ማንኛውም የቦርድ አባል በስብሰባ ማንኘት የማይችልበት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥመው ጉዳዩን ከስብሰባው ሶስት ቀን አስቀድሞ ለቦርድ ሰብሳቢ ማሳወቅ አለበት፡፡

7. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) ቢኖርም የቦርዱ አባላት በአዋጁ አንቀፅ 18 መሰረት ፕሮጀክቶችን በማጽደቅ ወደ ጨረታ እንዲገቡ ወሳኔ በሚሰጥባቸው ስብሰባዎች ላይ በአካል ማንኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም በአንድ ጊዜ ስብሰባ ወደ ጨረታ የሚገቡ ፕሮጀክቶችን ማፅደቅ ካልተቻለ ማንኛውንም ተስማሚ የኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘዴን በመጠቀም በሚደረግ ስብሰባ ወሳኔ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

8. እያንዳንዱ የቦርድ አባል አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፡፡

9. ማንኛውም የቦርዱ ወሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙት አባላት በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም የአባላቱ ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

10. ማንኛውም የቦርድ አባል ድምፅ በሚሰጥበት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ጥቅም ያለው ከሆነ ይህንኑ ለቦርዱ ሰብሳቢ በማሳወቅ በጉዳዩ ላይ ድምፅ ከመስጠት ራሱን ማግለል አለበት፡፡

11. ማንኛውም በቦርዱ ስብሰባ ላይ የሚሳተፍ ግለሰብ በቦርድ ስብሰባ አጋጣሚ ያወቀውን ወይም ያገኘውን መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 7. <u>የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል</u>

1. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል በአዋጁ አንቀጽ 12(2) መሰረት ለተዋዋዩ ባለስልጣን የሚሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

   ሀ/ ቦርዱ በመግአ እንዲያዙ ለወሰናቸው ፕሮጀክቶች ከተዋዋይ ባለስልጣን ጋር በመተባበር አስፈላጊ የትራንዛክሽን አማካሪዎች እንዲኖሩት እገዛ ያደርጋል፤

   ለ/ በፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ወስጥ ከፕሮጀክት ዝግጅት እስከ አፈጻጸም ሂደት ወስጥ በንቃት የሚሳተፍ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ተወካይ የሚሆን ባለሙያ ይመድባል፤

   ሐ/ በተዋዋይ ባለስልጣን የፕሮጀክት በድን ወስጥ የተመደበው የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ተወካይ የተጣለበትን ኃላፊነት በተገቢው ሁኔታ እንዲወጣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ይከታተላል፤

   መ/ የፕሮጀክት ስምምነትና የጨረታ ሰነዶች ዝግጅት ላይ ተዋዋይ ባለስልጣኑ በትራንዛክሽን አማካሪዎች በመደገፍ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፤ የሰነዶቹን ጥራት ያረጋግጣል፡፡

   ሠ/ ለፕሮጀክቱ የተመደቡ ትራንዛክሽን አማካሪዎች ለተዋዋይ ባለስልጣንና ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወቅታዊና መደበኛ ሪፖርት እያደረጉ መሆኑን ይከታተላል፤

   ረ/ የመግአ ፕሮጀክት ለአሸናፊው የግል ባለሀብት ከተላለፈ በኋላ የመግአ ፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን የፕሮጀክት ስምምነት ሰነዶችን በትክክል ሚዳታቸውን እንዲሁም

የፕሮጀክት ስምምነቱን ለሚፈጸም አስፈላጊ ድጋፍና እገዛዎች ማሰጡን ያረጋግጣል፡፡

2. የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የግል ባለሀብትን በሚመርጥበት ወቅት፡ –

ሀ/ በተዘጋጀው የፕሮጀክት ስምምነት ሰነድና እና የጨረታ ሰነድ በማጠቃም ማንኛውም የሚጣ ሂደት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ለ/ አግባብነት ያላቸው የተዋዋይ ባለስልጣን ፍላጎትና ጥያቄዎች በሁሉም የግል ባለሀብት ሚጣ ሂደቶች ወስጥ ግምት ወስጥ መግባታቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ/ ተዋዋይ ባለስልጣኑ የግል ባለሀብቱን በማሚጥ ሂደት ወስጥ ሚኑ ተሳትፎ እንዲኖረው ያመቻቻል፤ ሚተፉንም ያረጋግጣል፤

መ/ ከተወዳዳሪ የግል ባለሀብቶች ጋር በሚደረግ ወይይት ማሻነት በጨረታ ሰነዶች ላይ በሚኖር ማሻሻያ ላይ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ተሳትፎ አንዲያደርግ ያመቻቻል፤

## 8. ማኑዋሎች

1. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የመንግስትና የግል አጋርነት አተገባበርን ለማስለጥ የሚዘጋጃቸው ማንዋሎች ቢያንስ የሚከተሉትን ማስረታዊ ጉዳዮች ማካተት አለባቸው፡

   ሀ/ በመግአ ሊታቀፉ የሚችሉ ፕሮጀክቶች የሚለዩበትና የሚጣሩበትን መመዘኛ (Project Screening Criteria)፣

   ለ/ የአዋጭነት ጥናቶች የሚገመገሙባቸውን ማስኪያዎች (Project Feasibility and Appraisal Criteria)፣

   ሐ/ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘቱ የሚወሰንበትን መመዘኛ (Value for Money)፣

   መ/ የመንግስትን ድጋፍ ለማጠየቅ የሚያስችሉ ማስፈርቶች፣

   ሠ/ ሞዴል የፕሮጀክት ስምምነቶች ፣

   ረ/ የመግአ ኮንትራት አስተዳደር አሠራሮች፣

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የመግአ የፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም ግምገማ መሠረት በሚደረግ የሚዘጋጃቸውን ማኑዋሎች በየጊዜው ማሻሻል አለበት፡፡

3. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የሚዘጋጃቸውን ማኑዋሎች ለባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ ሚደረግ ይኖርበታል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት
# የተዋዋይ ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

## 9. ተዋዋይ ባለስልጣን

1. በመግአ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት ቦርዱ አንድን ፕሮጀክት በመግአ አሠራር እንዲተገበር ከፈቀደ በኋላ ተዋዋይ ባለስልጣን የመግአ ፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ያቋቁማል፡፡ የመግአ ፕሮጀክት አስተዳደር ቡድንን በማቋቋም ረገድ የተዋዋይ ባለስልጣኑ፡ –

ሀ/ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑን ለማቋቋም አስፈላጊ ድጋፍ እንዲሰጠውና እንዲሁም ተወካይ እንዲመደብለት የመንግስት ዳይሬክቶሬት ጀኔራልን ይጠይቃል፤

ለ/ ከራሱ ባለሞያዎች የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የሕግ እንዲሁም ፕሮጀክቱን ለማዘጋጀት፣ ለማስተዳደርና ለመተግባር ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሞያዎች ይመርጣል፣ ይመድባል፤

ሐ/ ለፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ከተመደቡት ባለሞያዎች መካከል በዋናነት የፕሮጀክት ዝግጅት ሥራዎች ላይ ውሳኔዎችን የሚሰጥ የፕሮጀክት አስተዳደደር ቡድን መሪ ይሰይማል፤

መ/ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለመንግስት ፕሮጀክት ስራ በመንግስት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ሲፈቀድ የመንግስት ትራንዛክሽን አማካሪዎችን ለመቆጣጠር የሚያስፈልገውን የፋይናንሻል፣ ቴክኒካልና የሕግ ክህሎት ያለውን ባለሞያ በመቅጠር ሊያሰራ ይችላል ወይም ተጨማሪ አማካሪ ሊቀጥር ወይም ሊመድብ ይችላል፡፡

2. ተዋዋይ ባለስልጣኑ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም ለማስለጥ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን በሚቋቋምበት ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሌሎች ቁልፍ ባለድርሻ ተቋማት ተወካይ ሊያካትት ይችላል፡፡ ባለሞያዎቹ ቋሚ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባል ሳይሆኑ ቴክኒካል ዕውቀታቸው ሲፈለግ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉ ሊደረግ ይችላል፡፡

3. ተዋዋይ ባለስልጣኑ በመንግስት አዋጅ መሰረት የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣቱን በየጊዜው በመከታተል ሊያረጋግጥ አለበት፡፡

4. ተዋዋይ ባለስልጣኑ በመንግስት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል በኩል የተላከለትን የፕሮጀክት ስምምነት ከመፈረሙ በፊት አስፈላጊ የሆኑ የማስፈቀድ ሥራዎችን የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

## 10. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን

1. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በመንግስት ፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት በየጊዜው ስብሰባ በማድረግ በፕሮጀክት አዋጭነት እና ሌሎች ጥናቶች እንዲሁም በፕሮጀክት ቅርፅ ዝግጅት፣ በፕሮጀክት ስምምነቶች ዝግጅት እና ጨረታ ሰነድ ዝግጅት እንዲሁም በስራ ላይ ባለው የመንግስት ፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ውይይት ማድረግ አለበት፡፡

2. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በሚያወጣው የስበስባ መርሀ ግብር መሰረት መሰብሰብ የሚችል ሆኖ ፡-

ሀ/ ሁሉም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት መገኘት እንዲችሉ የቡድን መሪው ቀደም ብሎ ስለሚኖሩ ስብሰባዎች በአግባቡ ማሳወቅ አለበት፤

ለ/ ሁሉም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት በሁሉም ውይይቶች ላይ በተከታታይ መሳተፍ ያለባቸው ሲሆን፤ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ለቡድን መሪው ማስታወቅ አለባቸው፤

ሐ/ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት የጥቅም ግጭት በፕሮጀክት ዝግጅትና ትግበራ ወቅት የሚኖር ከሆነ ወይም እንደሚኖር ከተገመተ ወይም እንዳለ ካወቁ ወዲያው ለቡድን መሪው በማሳወቅ በጉዳዩ ላይ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ የቡድኑን ምክር ወይም ውሳኔ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

3. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ እንደሁኔታው በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እና በትራንዛክሽን አማካሪዎች በሚታገዝ የጨረታ ሰነድ እና የፕሮጀክት ስምምነት ማዘጋጀት አለበት፡፡

4. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በትራንዛክሽን አማካሪዎች የተዘጋጁ ከፕሮጀክት ዝግጅት ጋር የተገናኙ ሰነዶችን ወይም የምክር ሀሳቦችን በማገምገም ለተዋዋይ ባለስልጣኑ ወይም ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያቀርባል፡፡

5. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት የተሰጣቸውን የፕሮጀክት መረጃዎች በሚስጥር የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

6. በመግአ አዋጅ ወስጥ ከተዘረዘሩት ኃላፊነቶች በተጨማሪ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ዕቅድ መሰረት እየሰራ መሆኑንና ተዋዋይ ባለስልጣኑም ሆነ የግል ባለሀብቱ በፕሮጀክት ስምምነቱ መሠረት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ለሚረጋገጥ የሚረዳ የፕሮጀክት አፈጻጸም መከታተያ ሰነድ ያዘጋጃል፤ የሰነዱ ይዘትና ጥራት በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እንዲረጋገጥ ይደረጋል፤ በሰነዱ መሰረት የተዘጋጀውን ሪፖርት ለተዋዋይ ባለስልጣንና ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያቀርባል፡፡

7. የፕሮጀክት ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ተዋዋይ ባለስልጣን እንደገና በፕሮጀክት ስምምነቱ ላይ መደራደር የሚያስፈልግበት ሁኔታ ቢያገጥም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን የድርድሩን አስፈላጊነትና ወጤት የሚያስከትለውን ለውጥ ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ማሳወቅ አለበት፡፡ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ ቁጥር 1(ሐ) መሠረት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይህንኑ ለቦርዱ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የመንግስትና የግል አጋርነት ዝግጅትና የሚጸደቅ ሂደት

### 11. ፕሮጀክቶችን የመለየት ስራ

1. በመሠረተ-ልማት ዕቅድ ወይም በህዝብ አገልግሎት ማስፋፋት ሂደት ወስጥ ከግል ባለሀብት ጋር በመግአ እንዲተገበሩ የሚያስፈልጉ ፕሮጀክቶችን፤ ተዋዋይ ባለስልጣን ወይም መንግስታዊ ተቋም ወይም የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በመለየት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በመግአ ስልት ሊተገበሩ የሚችሉትን ፕሮጀክቶች ዝርዝር በቅደም ተከተል ይይዛል፣ ከተዋዋይ ባለስልጣን ወይም ከሌሎች መንግስት ተቋማት የተገኘውን መረጃ በመጠቀም የፕሮጀክቶች ወቅታዊ መረጃ ይይዛል፡፡

3. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በመግአ እንዲያዙ የሚያስፈልጉ ፕሮጀክቶችን በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት በመለየት ለቦርዱ ይሁንታ በማቅረበው የመግአ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ወስጥ እንዲካተቱ በመወሰን ያቀርባል፡፡ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይህንን ሲያደርግ ለዚህ ተግባር የወጣውን የአሰራር ስርዓት ይከተላል፡፡

### 12. በቦርድ ስለሚሰጥ የቅድሚያ ፈቃድ

1. በመግአ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት ቦርዱ ማንኛውንም ፕሮጀክት በመግአ ሞዴል እንዲተገበር ሲፈቅድ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ወስጥ ያስገባል፡-

ሀ/ ፕሮጀክቱ ከኢትዮጵያ ልማት ፖሊሲ ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤

ለ/ ፕሮጀክቱ ለሚያስገኘው ምርት ወይም አገልግሎት በቂ ፍላጎት መኖሩን፣

ሐ/ ፕሮጀክቱ ትርጉም ያለው ህዝባዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን፤ በመንግስት ከሚያዝ ይልቅ በግሉ ዘርፍ ቢያዝ የተሻለ መሆኑንና እንዲሁም ተገቢውን የፕሮጀክት ስጋቶች ለግል ባለሀብቱ ለማስተላለፍ ዕድል የሚሰጥ መሆኑን፣

መ/ ፕሮጀክቱ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘቱን (Value for Money)፣

ሠ/ የሚጠበቀውን የመንግስት ድጋፍ ጨምሮ ለፕሮጀክቱ በቂ የፋይናንስ ሀብት ማቅረብ የሚቻል መሆኑን፣ እና

ረ/ ተዋዋይ ባለስልጣን ፕሮጀክቱን ለማዘጋጀት እና ተግባራዊ ለማድረግ በቂ ሀብትና አቅም ያለው መሆኑን፤

2. ቦርዱ ፕሮጀክቶች በመግአ እንዲተገበሩ ሲፈቅድ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሳይወሰን በፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት መሟላት ስለሚኖርባቸው ሁኔታዎች ሊወስን ይችላል፤

ሀ/ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ የመግአ ፕሮጀክትን በሚያዘጋጅበት ወቅት ሊከተላቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን፣

ለ/ በተዋዋይ ባለሥልጣን ስር ለሚቋቋም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ስለሚያስፈልገው የሰው ሀብትና የሙያ ስብጥር ፣

## 13. የአዋጭነት ጥናት

1. ተዋዋይ ባለስልጣኑ የአዋጭነት ጥናቱን የሚያዘጋጀው የመንግስትና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ባወጣው የመግአ ማኑዋል መሠረት ነው፡፡

2. በመግአ አዋጅ አንቀፅ 17 (2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች በተጨማሪ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን የሀገር ወስጥ የግል ባለሀብት በማንኛውም የመግአ ፕሮጀክት ላይ የሚሳተፍበትን አማራጭ ስለመኖሩ ይገመግማል፡፡

3. በአዋጭነት ጥናት ወጤት ማሰረት፣ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ከሚኒስቴሩና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር በመተባበር የመግአ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ታሳቢ የሆኑ ግዴታዎች ትንታኔ ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በማነጻጸርና ከፋይናንስ ግዴታዎች ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን በሚያሳይ ሜኑ ያዘጋጃል፡፡

4. ከተዋዋይ ባለስልጣን የሚቀርብ የመግአ አዋጭነት ጥናት፤ በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተገምግሞ ከወሳኔ ሀሳብ ጋር ለቦርድ ወሳኔ መቅረብ አለበት፡፡

## 14. ወደ ጨረታ ለመግባት በቦርዱ ስለማጽደቅ

1. በአዋጁ አንቀጽ 18 ማሰረት ተዋዋይ ባለስልጣን ለሚያከናወነው ፕሮጀክት የግል ባለሀብት ለማምረጥ ጨረታ እንዲወጣ በቦርዱ ለማፀደቅ በመግአ ማንዋል ማሰረት አዘጋጅቶ

ከሚቀርበው ደረጃወን የጠበቀ የአዋጪነት ጥናት በተጨማሪ የሚከተሉትን ሰነዶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡ -

ሀ/ ፕሮጀክቱን የሚፈፅመው የግል ባለሀብት የሚሟሟጥበትን የጨረታ ዕቅድ ጨረታው የሚፈፀምበትን ሂደት ከሚቀሳይ ሰነድ ጋር፣ የፕሮጀክቱ ስምምነት የሚመሰረትባቸውን ዋና ዋና የወል ቃሎችና ሁኔታዎች (Heads of terms for Project) ወይም የፕሮጀክት ስምምነቱን ረቂቅ ሰነድ፣

ለ/ የፕሮጀክት ስምምነቱ ከሚፈረሙ በፊት ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት የተሰጡ የፈቃድ ሰነዶች፣

ሐ/ የአዋጪነት ጥናቱ ከመጽደቁ በፊት እንደ ፕሮጀክቱ ባህሪ ሊረጋገጡ የሚገባቸው ልዩ ሁኔታዎች ካሉ በተዋዋይ ባለስልጣን በኩል ታይተው ስለሚረጋገጣቸው የሚገልጽ ሰነድ፤

2. የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ተዋዋዩ ባለስልጣን በቦርዱ እንዲጸድቅለት ያቀረበወን የአዋጪነት ጥናት በመገምገም ለቦርዱ በሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተሉት ነጥቦች መካተታቸውን ሚረጋገጥ አለበት፡ -

ሀ/ በተዋዋዩ ባለሥልጣን የቀረበው የአዋጪነት ጥናት አግባብነት ባላቸው ሰነዶች የተደገፈና በዚሁ መሰረት ፕሮጀክቱ በመገአ ሜቀፍ ቢሰራ የሚያዋጣ መሆኑን፤

ለ/ እንደፕሮጀክቱ ባህሪ የግል ባለሀብቱን ለማሚረጥ ተገቢ የሆነወን የግል ባለሀብት ማምረጫ ዘዴ ወይም የጨረታ ዕቅድ በተጨባጭ አስረጂ ነጥቦች ተደግፎ የቀረበ መሆኑን ፣

ሐ/ የግል ባለሀብቱ የሚሟሟጥባቸው ዋና ዋና የግምገማ መስፈርቶች እንዲሁም እንደአግባብነቱ የፕሮጀክት ስምምነቱ የሚመሰረትባቸውን መሰረታዊ የወል ቃሎችና ሁኔታዎች ማካተቱን፡፡

3. ፕሮጀክቱ በሚጸድቅበት ወቅት ተዋዋዩ ባለስልጣን በቦርዱ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ፕሮጀክቱን ለቦርዱ ማስረዳት እንዲሁም ከቦርዱ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ላይ ሜልስ የመስጠት መብት ይኖረዋል፡፡

4. የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የጨረታ ሂደቱን እንዲያካሄድ ሲፈቀድለት፣ በመገአ አዋጅ አንቀጽ 18 (4) መሠረት ቦርዱ ከሚሟከተው የመንግስት ተቋም የመንግስት ድጋፍ ወይም ዋስትና ማግኘቱን በሚረጋገጥ ጨረታውን እንዲያወጣ ካልፈቀደ በስተቀር የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ጨረታ ማውጣት አይችልም፡

5. በጨረታ ወቅት ወይም የፕሮጀክት ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ በድርድር የፕሮጀክቱ ቅርፅ ትርጉም ባለው ሜኩ የሚቀየር ከሆነ የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የተዋዋይ ባለስልጣኑን የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን በማሳተፍ የለወጡን ተፅዕኖ በሚያሳይ ሜኩ በጥልቀት ተንትኖ ለቦርዱ ውሳኔ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

## 15. የመንግስት ድጋፍ

ለፕሮጀክት ስምምነት በመገአ አዋጅ አንቀጽ 47 መሠረት የመንግስት ድጋፍ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲሁም በሕግ የተጣለ የመንግስት ድጋፍ በሚሟከተው የመንግስት ባለስልጣን የሚጸደቅ ግዴታ እስከሌለ ድረስ ቦርዱ በመገአ አዋጅ አንቀጽ 18 እና 32 መሰረት የመገአ

ፕሮጀክትን ሙሉ በሙሉ በራሱ ተፈላጊውን የማግስት ድጋፍ እንደሚስጸደቅ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## የግል ባለሀብትን ስለማሟረጥ

## 16. ብቃት ሚጋገጥ

1. ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም ከግል ባለሀብቱ የሚፈለገውን ብቃት ለማስታወቅና የተቻለውን ያህል ተጫራች ለማበዝ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ የጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ አንድ ጊዜ መውጣት ይኖርበታል፡፡ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይህንኑ ጥሪ በራሱ፣ በሚስቴር መ/ቤቱ እንዲሁም በተዋዋይ ባለስልጣኑ ድህረ-ገጽ ላይ ማውጣት አለበት ፡፡

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ከጋዜጣ ጥሪ በተጨማሪ ለመጫረት እንደሚችሉ ለይቶ ለሚያወቃቸው ተጫራቾች ጥሪውን በቀጥታ ሚላክ ይችላል፡፡

3. የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ይዘት ቢያንስ የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊያካትት ይገባል፡-

   ሀ/ ከፕሮጀክቱ ጋር የተገናኙ አጠቃላይ ሚጃዎችን፣

   ለ/ ለፕሮጀክቱ ማስረታዊ የሆኑ ጉዳዮች፣ ለምሳሌ ከፕሮጀክቱ የሚጠበቀው አገልግሎት እና ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገው ፋይናንስ የሚቀርብበት ሁኔታ፣

   ሐ/ የሚታወቅ ከሆነ የፕሮጀክት ስምምነቱ የሚያስረትባቸው ዋና ዋና የውል ቃሎች፣

   መ/ የቅድሙ-ብቃት ሚጋገጫ መስፈርቶች እና፣

   ሠ/ የብቃት ሚጋገጫ የሚቀርብበት አኳኋንና የመቅረቢያ ቀነ ገደብን፡፡

## 17. የቅድሙ-ብቃት ሚጋገጫ መስፈርቶች

1. በብቃት ሚጋገጫ ማጠየቂያ ወስጥ የሚካተቱ የቅድሙ-ብቃት ሚጋገጫ መስፈርቶች ቢያንስ የሚከተሉትን ነጥቦች ሊይዙ ይገባል፡፡

   ሀ/ በማንኛውም የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ደረጃ ሥራውን በአግባቡ ማከናወን የሚያስችል በቂ የሙያ እና የቴክኒክ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች መኖራቸውን፣

   ለ/ የፕሮጀክቱን የፋይናንስ አስተዳደር ማሟራት የሚያስችል ብቃት እና የፕሮጀክቱን የፋይናንስ ፍላጎት በዘላቂነት ማሟላት የሚያስችል አቅም፣

   ሐ/ አስፈላጊ አስተዳደራዊ እና ድርጅታዊ አቅም፣ አስተማማኝነት እና ልምድ፣ ቀደም ሲል ተመሳሳይ የመሰረተ ልማት ግንባታና የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች ላይ ያለን ልምድ ፡፡

2. የብቃት መመዘኛዎች በሚከተሉት መሰረት በማስረጃ ሚጋገጥ አለባቸው፡-

   ሀ/ የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የሥራ አመራር ብቃት በሚጠይቁ ተመሣሣይ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ቀዳሚ የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

   ለ/ የፋይናንስ አቅምን በተመለከተ የኩባኒያው የተጣራ ዋጋ (net worth)፣ የተጣራ ገቢ (net turnover) ወይም ሌሎች አስፈላጊ የፋይናንስ

ማስፈርቶች፣ በኦዲት የተረጋገጡ የሂሳብ መግለጫዎች ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው የፋይናንስ ሰነዶች ፤

ሐ/ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አስፈላጊ ናቸው ያላቸው ሌሎች ማስፈርቶች፤

3. ለዓይነተኛ የመግአ ፕሮጀክቶች በተለይ የሚያስፈልጉ የቅድሙ-ብቃት ሚጋገጫ ማስፈርቶች የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በሚያወጣው ማኑዋል ወስጥ በዝርዝር ይቀመጣሉ፡፡

## 18. የመወዳደሪያ ሀሳብ ስለማጠየቅ

1. በመግአ አዋጅ ወስጥ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የመወዳደሪያ ሀሳብ፡-

ሀ/ ማካተል የሚባወን የግል ባለሀብት አሜራረጥ ሂደት በግልፅ ማስቀመጥ አለበት፤

ለ/ እንዳስፈላጊነቱ ተጫራቾች በጨረታ ማቅረቢያ ነጥቦችና በፕሮጀክት ስምምነቶች ላይ አስተያየት የሚጠባትን ሂደት በግልጽ ማስየት አለበት፤

ሐ/ ተጫራቾች ማብራሪያ የሚጠይቁበትን ጊዜ እና ሂደት መግለጽ አለበት፤

መ/ ተጫራቾች ሊያሟሉ የሚባቸወን ማስረታዊ መመዛኛዎችና ሁኔታዎችን ማስየት አለበት፤

ሠ/ የቴክኒክና ፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አቀራረብ ወጥነት እንዲኖረው ሜድረግ አለበት፤

ረ/ የመወዳደሪያ ሀሳቡ የሚቅርብበትን ጊዜና ቦታ በግልጽ ማመልከት አለበት፤

ሰ/ ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ካሉ ተጫራቹ ሚጃ ወይም ማብራሪያ የሚያገኝበትን አድራሻ ማስቀመጥ አለበት፤

ሸ) የቴክኒክና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች የሚቀረቡበትን መንገድና የግምገማ ስርዓቱን ግልጽ ሜድረግ አለበት፡፡

## 19. የጨረታ ዋስትና

1. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተጫራቾች የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡ ማጠየቅ አለበት፡፡

2. የመግአ ዳሬክቶሬት ጄኔራል ለጨረታ ዋስትና የተጠየቀው ዓይነት፣ ቅርፅ፣ ማጠን እና ሌሎች ዋና ዋና ጉዳዮች በገበያ ልምድ ወስጥ የሚታወቁ መሆናቸወን ሚጋገጥ አለበት፡፡

3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናው ማጠን ተጫራቾች የተሳተፉበትን ጨረታ እንዲያከብሩ የሚያነሳሳ ሆኖ፣ የመጪቻ ዋጋ በማፍር ተሳታፊዎችን እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ወይም አላግባብ ለጨረታ ዝግጅት ተጫራቾች የሚያወጡትን ወጪ በማካር እንዳይሳተፉ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

4. አንድ ተጫራች ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ሊወሰደበት አይችልም፡-

ሀ/ የመወዳደሪያው ሀሳቡ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ የመጫቻ ሰነዱን ሜሎ በመወሰድ ከወድድሩ መውጣት ወይም ባቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ማሻሻያ ማድረግ፤

ለ/ በመንግአ አዋጅ አንቀጽ 31 መሠረት የመንግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አስፈላጊነቱን በማመን በሚያደርገው ጥሪ ማስረት ቀርቦ ድርድር ለማድረግ አለመቻል፣

ሐ/ ተጫራቹ አሸናፊነቱ ከተገለጸለት በኋላ የመንግስት የግል አጋርነት ስምምነትን እንዲፈርም ሲጠየቅ በተወሰነው ጊዜ ቀርቦ ሳይፈርም ቢቀር ወይም ፤

መ/ አሸናፊነቱ ከተገለጸለት በኋላ የፕሮጀክት ስምምነት ግዴታውን ለመወጣት የሚጠየቀውን የሥራ አፈፃፀም ዋስትና ያላቀረበ እንደሆነ ወይም የፕሮጀክት ስምምነቱ ከሚፈረሙ በፊት በመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ የተገለፀውን ሌላ ማናቸውንም ቅድመ ሁኔታ ያላሟላ እንደሆነ፣

## 20. የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ስለማምገም

1. የቴክኒካዊ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ እና የማወዳደሪያ ማስፈርቶች ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፤

   ሀ/ ቴክኒካዊ ብቃት፤

   ለ/ ከአካባቢ ጥበቃ መመዘኛዎች ጋር መጣጣም፤

   ሐ/ ሊተገበር የሚችል መሆኑ፤

   መ/ የአገልግሎቱን ወይም ምርቱን ጥራት እና ቀጣይነት ለሚጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያካተተ መሆኑ፤

2. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማምገምና ለማወዳደር የሚዱ ማስፈርቶች በፕሮጀክቱ ዓይነት ላይ የተመሰረቱ ይሆናል፡፡ የመንግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ለዚህ አፈፃፀም ዝርዝር ማኑዋል ያወጣል፡፡

3. የሀገር ወስጥ ተሳትፎን ለማበረታታት ሲባል የሀገር ወስጥ ባለሀብት የካፒታል ድርሻ ከ 50% የሚበልጥ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ በመንግአ ፕሮጀክት ማሳተፍ ለሚፈልግ ኩባንያ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቡት የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ ነጥብ ወስጥ እስከ 7% (ሰባት በመቶ) ልዩ አስተያየት እንደሚደረግ በመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ጥሪ ሊገለጽ ይችላል፡፡

   ሀ/ ግንባታን የሚያካትት ፕሮጀክት ሲሆን ቢያንስ 30% ጥሬ ዕቃ ከኢትዮጵያ የሚጠቀም ከሆነና ከጠቅላላ ሰራተኞቹ 50% ኢትዮጵያዊያን ሰራተኞችን ከሆኑ፤

   ለ/ በኩባንያው አመራር ከሚሳተፉት ሰዎች ከ50% የሚያንሱት ኢትዮጵያዊን ሲሆኑ ፡፡

   ሐ/ ግንባታን የሚያካትት ፕሮጀክት ሲሆን እንደ ፕሮጀክቱ ዓይነት የልዩ አስተያት ተጠቃሚ ለመሆን የሚጠየቀው ማስፈርት በመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ጥሪ የሚወሰን ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 የተማለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ከአገር ወስጥ ባለሀብቶች ጋር ጥምረት የሚፈጥሩ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## 21. አሸናፊወን ስለማሳወቅና ስምምነት ስለሚፈረም

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 30 መሠረት የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ስለጨረታው ወጤት ለተጫራቾች ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ተዋዋይ ባለስልጣን የፕሮጀክት ስምምነት ሚፈረም የለበትም፡፡

2. የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት በሚፈረምበት ወቅት የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የጨረታወን ወጤት በሀገር ደረጃ በሚሰራጭ ጋዜጣና አመቺ በሆነ የህዝብ መገናኛ ሚዲያ የኮንትራቱን ዓላማ፣ የተዋዋዮቹ ስም፣ የክፍያው ሁኔታና ዋና ዋና የስምምነቱ ገጽታዎችን ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡ የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ይህን ሚደጃ በራሱና በሚስቴሩ ደህረ-ገጽ ላይ ያወጣል፡፡

3. የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል እና ተዋዋይ ባለስልጣን ተጫራቾችን በመምረጥ ወል የማስጠት ሂደትን በተማለከተ ተገቢወን ሚደጃ ማያዝ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## በወድድር ላይ የተመሠረተ ወይይት

## 22. በወድድር ላይ የተመሠረተ ወይይት ለማጠቀም ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች

በመንግሥት አዋጅ አንቀጽ 37 (1) መሰረት በወይይት ላይ የተመሰረተ ወድድርን ለማጠቀም አንድ ፕሮጀክት ወስብስብ ነው የሚባለው ተዋዋይ ባለስልጣኑ እና የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ፡-

1. የየራሳቸወን ፍላጎት ወይም ዓላማ ለማሟላት ወይም ለማሳካት ማጠቀም ስለሚያርባቸው ቴክኒካዊ ዘደዎችን በተጨባጭ አብራርተው ማቅረብ ካልቻሉ እና/ወይም

2. የፕሮጀክቱን ሕጋዊ እና/ወይም የፋይናንስ ስርዓት በተጨባጭ መወሰን ያልቻሉ ሲሆን ነው፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ቀጥታ ድርድር

## 23. ለቀጥታ ድርድር ሊሟሉ የሚገቡ ቅድሙ-ሁኔታዎች

በመንግሥት አዋጅ በአንቀጽ 39 የተደነገጉትን ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በመንግሥት አዋጅ አንቀፅ 39 ንዑስ ቁጥር 1(ለ) እና (ረ) መሠረት የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል በቦርድ ሲፈቀድ በመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት ላይ በቀጥታ ለሚደራደር የሚከተሉትን ቅድሙ-ሁኔታዎች ማሟላት አለባቸው፡፡

1. ፕሮጀክቱ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጊዜ ወስጥ የሚጠናቀቅ እና ያስከትላል ተብሎ የሚገመተው የመነሻ ኢንቨስትመንት ወጪ ከመቶ አርባ ሚሊዮን ብር የሚበልጥ ከሆነ፤

2. ፕሮጀክቱ ከኢንዱስትሪያል እና ከሌላ የኢንቨስትመንት ስራ ጋር ተያያዥ ከሆነ እና አገልግሎቱ በኢንዱስትሪ ወይም የኢንቨስትመንት ስራው በተሰማራው ባለሀብት መካከል ያለበትና ሌሎች ተጫራቾች በፕሮጀክቱ የመሳተፍ ፍላጎት ይኖራቸዋል ወይም በፕሮጀክቱ የሚተፋበት የተሻለ አማራጭ ይዘው ይቀርባሉ ተብሎ የሚታመን ሲሆን ነው፡፡ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል አቅም ያላቸው የግል ባለሀብቶች ፍላጎታቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ፣ የመወዳደሪያ ዋጋ ወይም ሌሎች ፍላጎቶችን እንዲገልጹ የጋበዛቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃና የተሰጠውን ምላሽ በመተንተን ለመግአ ቦርድ ያቀርባል፡፡ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል በተመሳሳይ የፕሮጀክት ስራ ላይ ልምድ ካላቸውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዋቂ ከሆኑ ቢያንስ ከሶስት ያላነሱ ድርጅቶች ጋር ቀደም ብሎ ግንኙነት ማድረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## <u>በራስ ተነሳሽነት የሚቀርብ የፕሮጀክት ሀሳብ</u>

### 24. <u>በራስ ተነሳሽነት የፕሮጀክት ሀሳብ ካቀረበ የግል ባለሃብት ጋር ስለሚደረግ የመጀመሪያ ስምምነት</u>

1. በራስ ተነሳሽነት የቀረበው የፕሮጀክት ሀሳብ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 43 (1) መሰረት በመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ተቀባይነት ካገኘ ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብትና ተዋዋዩ ባለስልጣን በመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ድጋፍ ፕሮጀክቱ ለቦርዱ ከመቅረቡ በፊት ከቀረበው ሀሳብ ጋር በተያያዘ ሀሳብ አቅራቢው ባለሀብትና የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ ስምምነት ይገባሉ፡፡ ይህ ስምምነት ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

   ሀ/ በሀሳብ አቅራቢው የተዘጋጀውን ጥናት ይዘት ምስጢር ስለማጠበቅ፣

   ለ/ ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብት ጨረታውን ያላሸነፈ እንደሆነ የፕሮጀክት ጥናቱን መብቶች ለተወያዩ ባለስልጣን ወይም ለሌላ ወገን ስለሚተላለፍበት መንገድና ሁኔታ ፤

   ሐ/ ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብት ጨረታውን ያላሸነፈ እንደሆነ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 43(4) መሰረት ጥናቱን ለማካሄድ ላወጣው ወጪ ስለሚከፈል የገንዘብ ካሳ ወይም በጨረታው ግምገማ ለሀሳብ አቅራቢው ስለሚሰጥ ተጨማሪ ነጥብ ፤ እና

   መ/ ፕሮጀክቱን ለማዘጋጀት ስመውሰዱ አስፈላጊ የሆኑ ቀጣይ እርምጃዎችን ማሳየትና ኃላፊነትን ስለመደልደል፣

2. የማአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የዚህን አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (1) ለማስፈጸም የሚያስችል የስምምነት ሞዴል ያዘጋጃል፡፡

## 25. ስለ ሚበረታቻ ነጥብ እና የወጪ ማካካሻ ገንዘብ

1. ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብት ማንነት፣ የተጨማሪ ነጥብ አሰጣጥ ዝርዝር ወይም ሀሳቡን ላቀረበው የግል ባለሀብት ሊሰጠው ስለሚችለው የካሳ ማጠን በወድድር ጨረታ ስነ-ሥርዓት ሰነድ ወስጥ ማለጽ ያለበት ሲሆን፣ የቅድሙ-ብቃት ሚጋገጫ የሚካሄድ ከሆነ ይኸው በዚህ ጊዜ ወስጥ ቢገለጽ ይሚጣል፡፡

2. ሀሳቡን ላቀረበው የግል ባለሀብት በጨረታው ወድድር ሂደት ሊሰጠዉ ስለሚባው ትክክለኛ የቴክኒክ ወይም የፋይናንስ መዉዳደሪያ ተጨማሪ ነጥብ መወሰን አስቸጋሪ መሆኑን ከግምት ወስጥ በማስገባት የማአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ሀሳቡን ላቀረበው ተወዳዳሪ የሚጠወን ተጨማሪ ነጥብ ወይም በአሸናፊነት ባይሚጥ የሚከፈለወን የወጪ ማካካሻ ገንዘብ ማጠን የመወሰን ስልጣን አለው፡፡

3. ለሀሳብ አቅራቢው ባለሀብት የሚከፈል የወጪ ማካካሻ ክፍያ ከአሸናፊው ተጫራቹ ጋር በሚደረገው የፕሮጀክት ስምምነት የሚወሰነው ለፕሮጀክቱ የሚወለው የፋይናንስ ማቅረቢያ ቀነ ገደብ ከማለፉ እና የፕሮጀክቱ ትግበራ ከመጀመሩ በፊት በፕሮጀክቱ ስምምነት እንደ ቅድመ ሁኔታ ተወስዶ ጨረታወን ባሸነፈው የግል ባለሀብት እንዲከፈል መደረግ አለበት፡፡ ይህ ግዴታ በመዉዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ወስጥ በግልጽ ማጠቀስ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት ይዘትና አፈጻጸም

## 26. የስምምነት ጊዜ

1. በአዋጁ አንቀጽ 45 ማሰረት በመንግስትና በግል አጋርነት የሚካሄድ ፕሮጀክት የቆይታ ጊዜ እንደፕሮጀክቱ ዓይነትና ባህሪ የሚወሰን ሆኖ ከሃያ እስከ ሠላሳ ዓመት ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የፕሮጀክቱ ልዩ ሁኔታ የሚጠይቅ ሲሆን ከሃያ ዓመት በታች የሚቆይ የፕሮጀክት ስምምነት ሊደረግ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የፕሮጀክት የቆይታ ጊዜ ሲወሰን የፕሮጀክቱን ሀብት የአገልግሎት ዘመን፣ፕሮጀክቱን በቀጣይነት ለማስኬድ የሚያስችል የፋይናንስ አቅርቦት መኖሩን እንዲሁም በአለም አቀፍ የገበያ ተሞክሮ ለተመሳሳይ ፕሮጀክቶች የሚጠው የቆይታ ጊዜ ከግምት ሊወሰድ ይገባል፡፡

## 27. የፕሮጀክት ሀብቶችን ስለማስተላለፍ

የፕሮጀክት ስምምነት ስምምነቱ ከወል ጊዜው አስቀድሞ ሲቋረጥ ወይም የስምምነት ጊዜው ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ሀብቶች ወደ ተዋዋይ ባለስልጣን ወይም ሌላ የመንግስት ተቋም የሚተላለፍበትን ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የፕሮጀክት ስምምነቱ ተዋዋይ ባለስልጣኑ ወይም ሌላ የመንግስት ተቋም የፕሮጀክቱ ሀብቶች በአገልግሎት ምክንያት የሚከተል

እርጅናን ከግምት ወስጥ በማስገባት የፕሮጀክቱ ሀብቶች በጥሩ ሁኔታ የሚተላለፉበትን አኳኋን የሚያረጋግጥበትን መንገድ መወሰን ይኖርበታል፡፡

## 28. የፕሮጀክት ስምምነት ስለሚቋረጥ

የፕሮጀክት ስምምነት የስምምነቱ ፍሬ ነገር መጣስ፣ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲጠር፣ የክፍያ ግዴታን ያለመወጣት ወይም በፕሮጀክት ስምምነቱ የሚወሰኑ ሌሎች እንደአግባብነቱ ፕሮጀክቱን ሊያቋርጡ የሚችሉ ወይም እንዲቋረጥ የሚያስገድዱ ሁኔታዎችን ሊወስን ይገባል፡፡

## ምዕራፍ አስር
## የመንግስትና የግል አጋርነት የስነ-ምግባር ደንቦች

## 29. ስነ-ምግባር

1. በመንግስትና የግል አጋርነት የተሰማሩ ሠራተኞች የሚከተሉትን የስነ ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ያከናወናሉ፡-
   - ሀ/ የተፈጠረ ወይም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ እና ራስን ከሂደቱ የማግለል፤
   - ለ/ ለዕጩ ተወዳዳሪና ፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብቶች እኩል የመወዳደርና የመፈጸም እድል ማስጠት፤
   - ሐ/ በስራ አጋጣሚ ያወቃቸውን የመንግስት ፕሮጀክቱን፣ የተወዳዳሪ ወይም የፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብቱን ሚስጥሮች በሚስጥር ማጠበቅ፤
   - መ/ ከዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብት የሚቀርብን የገንዘብ ዋጋ ያለውን ስጦታ ፣ አገልግሎት ወይም የቅጥር ዕድል አለመቀበል፤
   - ሠ/ በስራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የማሳወቅ እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፤
   - ረ/ ለህዝብ ሀብትና ንብረት ተቆርቋሪ መሆን፡፡

2. ማንኛውም ተወዳዳሪ የግል ባለሀብት የመንግስትና የግል ባለሀብት ሚጣ እና አፈጻጸም ሊያዛባ ከሚችል ከማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡ ስለሆነም፡-
   - ሀ/ የመንግስት መስሪያ ቤቱን ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ተግባር ወይም ወሳኔ ለማዛባት ወይም ከግል ባለሀብቱ ሚጣ እና የፕሮጀክት አፈጻጸሙ ጋር በተያያዘ መስሪያ ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሰራር ለማስለወጥ በማንኛውም መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ አለማስጠት ወይም ስጦታ ለማስጠት ቃል አለመግባት ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለማስጠት፤
   - ለ/ የመንግስት ፕሮጀክት የግል ባለሀብት ሚጣ ወይም አፈጻጸምን ለማዛባት በማሰብ የሀሰት ማስረጃ አለማቅረብ ወይም መግለጽ የነበረበትን ሚጃ አለመደበቅ፤

ሐ/ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሀሰት ወድድር አለማድረግ፤

መ/ በስራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የማሳወቅ እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ፤

ግዴታ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አስራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 30. ቅሬታዎች

1. የግል ባለሀብት ሲመረጥ በተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር የመንግሥት አዋጅን እና ይህንን መመሪያ ይጥሳል ብሎ የሚያምን ተወዳዳሪ የግል ባለሀብት ለመንግሥት ዳይሬክተር ጀኔራል ወይም በደረጃ ለቦርድ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንድ (1) በተደነገገው መሰረት አቤቱታ ሊቀርብባቸው አይችልም፦

ሀ/ በመንግሥት አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሚከናወን የግል ባለሀብት የመምረጫ ዘዴዎች፤

ለ/ በመንግሥት አዋጅ መሰረት ጨረታን ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብን ውድቅ ማድረግ፤

3. ተዋዋዩ ባለስልጣን በጨረታው ከተመረጠው የግል ባለሀብት ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ከፈረመ በኃላ ሂደቱ ከዚህ ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በመንግሥት

ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም በተዋዋዩ ባለስልጣን በተከናወኑ ወይም ሳይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በመንግሥት ዳይሬክተር ጀኔራል ወይም በቦርዱ ሊታዩ አይችሉም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሶስት (3) የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፦

ሀ/ በዚህ መመሪያ በተወሰነው የግዜ ገደብ ወስጥ ለመንግሥት ዳይሬክተር ጀኔራል አቤቱታ ሳይቀርብ የፕሮጀክት ስምምነት የተፈረመ ከሆነ፤

ለ/ አቤቱታው ቀርቦ መንግሥት ዳይሬክተር ጀኔራል ምላሽ ከሰጠ እና አቤቱታ አቅራቢው በዚህ መመሪያ በተወሰነው የግዜ ገደብ ወስጥ የመንግሥት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል በሰጠው ወሳኔ ላይ ለቦርዱ አቤቱታውን ሳያቀርብ የፕሮጀክት ስምምነት የተፈረመ ከሆነ፡፡

5. በመንግሥት የግል ባለሀብት ሚጣ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በፍታሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተቀመጡትን የአቤቱታ ስሚ ሥነ-ሥሂዓት ደንቦች በጥብቅ መከተል ሳያስፈልግ ቀለል ባለ ሥነ-ርዓት ይታያሉ፡፡

## 31. ለመንግሥት ዳይሬክተር ጀኔራል ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

1. በመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም በተዋዋዩ ባለሥልጣን በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለመገአ ዳይሬክተር ጀኔራል ነው፡፡

2. እጩ ተወዳዳሪ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መነሻ የሆነውን ወሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) የስራ ቀን ጊዜ ወስጥ ይሆናል፡፡

3. አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የመገአ ዳይሬክተር ጀኔራል የግል ባለሀብቱን ሚጣ ሂደት በማገድ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በአስር (10) የስራ ቀናት ጊዜ ወስጥ፤ ወሳኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ የጽሁፍ ወሳኔ ማስጠት አለበት፡፡

4. የመገአ ዳይሬክተር ጀኔራል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሶስት (3) በተወሰነው ጊዜ ወሳኔ ካልሰጠ ወይም አቤቱታ አቅራቢው የመገአ ዳይሬክተር ጀኔራል በሰጠው ወሳኔ ያልረካ እንደሆነ የመገአ ዳይሬክተር ጀኔራል ወሳኔ ለአቤቱታ አቅራቢው ማለጽ ከነበረበት የሚጨረሻ ቀን ወይም ወሳኔ የሰጠ ከሆነም ወሳኔው ከተገለጸለት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ሰባት (7) የስራ ቀን ጊዜ ወስጥ ለቦርዱ አቤቱታው ሊቀርብ ይችላል፡፡

## 32. ለቦርዱ ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. ቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብለት ወዲያውኑ ለመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል እና/ወይም ለተዋዋዩ ባለሥልጣን አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ በጽህፈት ቤቱ በኩል ይልካል፡፡ የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ቦርዱ ወሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በጉዳዩ ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት፡፡

2. ቦርዱ የእጩተወዳዳሪውን አቤቱታ ወድቅ ካላደረገው በስተቀር፡-

   ሀ/ የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ወሳኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ፤

   ለ/ የግል ባለሀብቱን ከመምረጥ ወይም የፕሮጀክት ስምምነት ከሚፈረም ጋር ከተያያዙ ወሳኔዎች በስተቀር የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ስራውን እንዲያከናውን፤

   ሐ/ የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ከሕግ ውጭ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ወሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ወድቅ እንዲሆን፣

   ወሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3. ቦርዱ በአቤቱታው ላይ ወሳኔ ከማስጠቱ በፊት ስለአቤቱታው ማወቅ ለሚገባቸው አካላት ማሳወቅ፣ ከነዚህም አካላት የቀረበ ሚጃ እና ማብራሪያ ሀሳብ ካለ ይህንኑ መመርመር አለበት፡፡

4. ቦርዱ አቤቱታ ከቀረበለት ቀን አንስቶ በሃያ አንድ (21) የስራ ቀናት ወስጥ ለወሳኔው ማስረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱትን የመፍትሄ እርምጃዎች በመጥቀስ ወሳኔ ማስጠት አለበት፡፡

## 33. በመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም በተዋዋይ ባለስልጣን ለቦርዱ ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. በግል ባለሀብት ሚጣ ሂደት የመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም ተዋዋይ ባለስልጣኑ ከተወዳዳሪ ወይም ከፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብቱ ሕገ ወጥ ድርጊት ወይም ሕጋዊ ጥቅሙን የሚጎዳ ድርጊት ተፈጽሞበኛል ብሎ ሲያምን በጨረታ ሰነዱ ወይም በስምምነት ሰነዱ ማስረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉዳዩን ለቦርዱ በጽሁፍ ያቀርባል፡፡

2. ቦርዱ ከመገአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ወይም ከተዋዋዩ ባለስልጣን አቤቱታ ሲቀርብለት አቤቱታ የቀረበ ማሆኑን እና የአቤቱታውን ፍሬ ሀሳብ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ አቤቱታ ለቀረበበት ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ለፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብት ይልካል፡፡

3. ቦርዱ አቤቱታውን ለመመርመር እና ወሳኔ ለማስጠት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ጠርቶ ማነጋገር ወይም ሚጃ ማጠየቅ እና

ማግኘት እንዲሁም ከማንኛውም አካል የሙያ ድጋፍ ማጠየቅ እና ማግኘት ይችላል፡፡

4. ቦርዱ የቀረበለትን አቤቱታ በተገቢው በመመርመር አቤቱታው በቀረበለት በሃያ አንድ (21) የስራ ቀናት ጊዜ ወስጥ ወሳኔ ይሰጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አራት (4) ማስረት ቦርዱ የሚሰጠው ወሳኔ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡ -

ሀ/ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ተዋዳዳሪ ወይም ፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብት በማንኛውም የመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክት ወድድር ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይሳተፍ ማገድ፤

ለ/ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ማስጠት፤

ሐ/ የቀረበውን አቤቱታ ወድቅ ማድረግ፤

## 34. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስትሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 35. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ___________ ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አብርሃም ተከስተ (ዶ/ር)**

**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሚኒስትር**

**__________ ቀን 2010 ዓ.ም**

**<u>አዲስ አበባ</u>**